# እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1-28/2018 የነበረው

# የአየር ጠባይ ግምገማ


ባለፈው የፌብርዋሪ ወር በመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት በበአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ የቆየ ሲሆን፤ ከሁለተኛዉ አስር ቀናት አጋማሽ ጀምሮ እስከ ወሩ መጨረሻ ድረስ የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ከዕለት ወደ ዕለት በመጠናከራቸው በተለይም በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እና በጥቂት ቦታዎች ላይ ደግሞ ከባድ ዝናብ እንዲኖር አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በወራቤ 58.8፣ በጂንካ 46.2 እና 33.1፣ በዳሊፋጂ 46.0፣ በጃራ 39.5፣ በተርጫ 38.6፣ በአርጆ 38.2 እና 36.4፣ በቡርጂ 35.5፣ በዲላ 32.7፣ በቁሉምሳ 30.9፣ በጊኒር 39.0፣ በሆሳዕና 30.5፣ እና በማጀቴ 30.6 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ ባለፈዉ የፌብርዋሪ ወር ምሥራቅ ትግራይ፣ ምሥራቅ አማራ፣ አብዛኛው ኦሮሚያ፣ጋምቤላ እና የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በተለያዩ ቦታዎቻቸው ላይ ዝናብ ነበራቸው።


ባለፈው ወር የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ25-128 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም፣ ደቡብ ወሎ እና ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሸዋ፣ አርሲና ባሌ፣ ጉጂና ቦረና እንዲሁም የደቡብ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ አዲስ አበባን ጨምሮ ከ5-14 ቀናት ያህል የዘነበ ሲሆን፤ ከትግራይ ደቡብና ምስራቅ ትግራይ፤ ከአማራ ምዕራብ ጎጃም፣ ደቡብና ሰሜን ጎንደር፣ አገዋዊ፣ ዋግህምራ፣ እንዲሁም ሰሜን ወሎ፤ ከአፋር ዞን 3 እና ዞን 5፤ ከኦሮሚያ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሸዋ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፤ ከሶማሌ ጅግጅጋ፣ የደገሀቡር ዞኖች ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፣ እንዲሁም ድሬዳዋና ሐረሪ ክፍሎች ደግሞ ከ5-25 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-5 ለሚሆኑ ቀናት ያህል አግኝተዋል (ካርታ 6 እና 7) ።

ባለፈው ወር የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር ከትግራይ የመካከለኛው ትግራይ ኪስ ቦታዎች እና ደቡብ ትግራይ፤ አብዛኛው አማራና ኦሮሚያ፤ ደቡብ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ ከጋምቤላ የዞን1 ክልል፤ ከሶማሌ የደገሀቡር ዞን እንዲሁም ሀረሪ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ደግሞ ከመደበኛው በታች የሆነ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 8) ።


ካርታ 6  እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 28 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



## ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 28 /2018 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 28 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1-28/2018 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው  ተፅዕኖ

ባለፈው የፌብርዋሪ ወር በተለይም በመጀመሪያውና በሁለተኛው አሥር ቀናቶች በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ የቆየ ሲሆን ይህም ሁኔታ ለበልግ ማሳ ዝግጅት አሉታዊ ተፅእኖ ነበረው፡፡ በሶስተኛው አሥር ቀናት ግን በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ የተስፋፋ ዝናብ እንደነበር እና ለበልግ ለማሳ ዝግጅት ጥሩ አጋጣሚ ነበር:: ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም በሰሜን ወሎ፤ በጅማ፣ በሰሜን ሸዋ፣ በቦረና፣ በአዲስ አበባ ፤በሰገን ህዝቦች፤በኢሉ-አባቦራ፣በምስራቅ ሸዋ ፣ በአርሲ፣ በባሌ ፤ በደቡብ ወሎና በምስራቅ ጎጃም፤ በደቡብና ምስራቅ ትግራይ፣ በድሬዳዋና ሐረሪ እንዲሁም በጅግጅጋ የተሻለ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የበልግ እርሻን ቀደም ብለው ለሚጀምሩ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅትና ለዘር ጊዜ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ እንዲሁም ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች ለሚገኙ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለመጠጥ ውሀና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት እንዲሁም ለቋሚ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 9)።


ካርታ 9    እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1-28/2018 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደርው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 1-28 ፌብሪዋሪ 2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ በተመለከተ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ በጥቂት የላይኛውና የመካከለኛው አባይ፣ የላይኛውና የታችኛው ስምጥ ሸለቆና ኦሞ ጊቤ፣ የላይኛው ባሮ አኮቦ፣ አዋሽ፣ እንዲሁም በጥቂት የታችኛው ግናሌዳዋ ከፊል ደረቅ እስከ መጠነኛ እርጥበት ሁኔታ ተስተውሏ፡፡ የተቀሩት ተፋሰሶች ከከፊል ደረቅ እስከ ደረቃማ ሁኔታ ተፅዕኖ ስር ነበሩ (ካርታ 10)፡፡

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከማርች 1-31/2018 የሚኖረው
## የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ ከቀደመው ወር በተሻለ ሁኔታ በማርች ወር የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች መደበኛ ቦታዎቻቸውን እየያዙና እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ጊዜ ሲሆን፤ በተለይም በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ከሚፈጠሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ዝናብ ይኖራል።

በሚቀጥለው ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛው እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ የሚጠበቅ ቢሆንም፤ በወሩ ውስጥ ወደ ሀገሪቱ ሊገባ በሚችለው እርጥበታማ አየር መጠን መቀነስ ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ ደረቃማ ቀናት ሊዘወተሩ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

<u>በአጠቃላይ በሚቀጥለው ወር ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ወለጋ፣ ሰሜን ሸዋ፣ የአርሲና የባሌ፣ የቦረናና የጉጂ ዞኖች እንዲሁም የምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ ፤ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋና ሐረርጌ፤ ከአፋር ዞን 3 እና 5፤ ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ዋግ ህምራ፣ሰሜን ሸዋ፣ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ ደቡብ ጎንደር፣ የባህዳር ዙሪያ፤ ጋምቤላ፤ ከትግራይ ክልል የመካከለኛ፣ የምሥራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል ጅጅጋ ፣ ሽንሌ፣ አፍዴር፣ ደጋሀቡርና ጎዴ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሁሉም ዞኖች፤ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና በጥቂት ሥፍራዎች ላይ ደግሞ ከመደበኛው በላይ ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ከባድ ዝናብ ያገኛሉ። የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።</u>

## እ.ኤ.አ ከማርች 1-31/2018 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የማርች ወር የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች መጠናከር እያሳየ የሚሄድበትና የወቅቱ ዝናብ በበልግ አብቃይ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚጠናከርበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለበልግ እርሻ ሥራ የማሳና የዘር ዝግጅት የሚካሄድበት ወቅት ነው፡፡ የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ መረጃ እንደሚያሳየው በሚቀጥለው ማርች ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛው እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ ይጠባቃል፡፡ ይህም ሁኔታ ለበልግ አብቃይ

አከባቢዎች ለበልግ እርሻ ሥራዎች፣ ለአፈር እርጥበት መጠናከርና ለዘር መዝራት አወንታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡ ሆኖም በወሩ ውስጥ ወደ ሀገሪቱ ሊገባ የሚችለው እርጥበታማ አየር መጠን በየጣልቃው እንደሚቀንስ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ ደረቃማ ቀናት ሊዘወተሩ ይችላሉ፤ ይህም ሁኔታ በበልግ እርሻ ዝግጅትና ዘር ለመዝራት ምቹ የሆኑ ሁኔታዎችን መፍጠር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሩ የተገኘውን እርጥበትና የዝናብ ውሃን በማቆር እንዲጠቀም ይመከራል፡፡

## እ.ኤ.አ ከማርች 1-31/2018 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው ማርች ወር መደበኛው የበልግ ወቅት ዝናብ በአብዛኛው የበልቅ ተጠቃሚ አካባቢዎች የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ የትንበያ መራጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ በሚቀጥለው ወር የበልግ ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑ ተፋሰሶች የተሻለ እርጥበት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ በተለይም የላይኛውና የመካከለኛው አባይ፣ የታችኛው ተከዜ፣ የመካከለኛውና የላይኛው ሪፍት ቫሊ፣ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ፣ ኦሞ ጊቤ እና አብዛኛው አፋር ደናክል ተፋሰሶች መጠነኛ የሆነ እርጥበት ሊያገኙ የሚችሉ ሲሆን፤ የተገኘውን የውሃ መጠን በአግባቡ መጠቀም ተገቢ ይሆናል፡፡